# ኦቲዝም (Autism)

ኦቲዝም አንዳንድ ጊዜ ትምህርት የመቀበል ወይም የአእምሮ ችግር ያለባቸውን ሰዎች የሚገልጽ ነው።

ኦቲዝም ብዙ ቅርጾች ያሉት በመሆኑ በዙርያው የሚገኙ ሰፊ ሁኔታዎችን ያጠቃልላል።

በዚህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ የሚገኙ ሰዎች በጋራ የሚያሳዩት ባህሪ፦

- ከሌሎች ሰዎች ጋር ግንኑነትን ለመፍጠር መቸገር
- ማህበራዊ ግንኙነትን መፍጠር አለመቻል
- ከሰዎች ጋር አለመግባባትና ርህራሄን አለማሳየት

ልጆች አልፎ አልፎ በትምህርት ቤት ውስጥ ችግሮች ይገጥሙአቸዋል፡ ይናደዳሉ፣ ደንቦችንና ህጎችን አይረዱም። ጓደኛ የማፍራትም ችግር አለባቸው።

ኦቲዝም አብሮ የሚወለድና ዕድሜ ልክ ሁኔታ ሲሆን በቅድምያ ሊያሳይ የሚችለው ምልክት ለመናገር መማር ያለመቻልን ወይም ባልተለመደ ሁኔታ መናገርን መማር ይሆናል። ለምሳሌ የተባለን ነገር ደግሞ ማለት ወይም የቴሌቪዥን ማስታወቂያን አድምጦ ማስተጋባት ዓይነት ማለት ነው።

በርካታ በኦቲዝም አጠቃላይ ሁኔታ ላይ (ስፔክትረም ኮንዲሽን) የሚገኙ ሰዎች ከሚገባው በላይ የሚሰጉና የሚጨነቁ ሲሆን በየዕለቱ የሚያከናውኑአቸውም ተግብራት እንዲለወጡባቸው አይፈልጉም።

አስበርገስ ሲንድሮም (Aspergers Syndrome) የኦቲዝምን ቅርፅ የያዘ ሲሆን አልፎ አልፎ High Functioning Autism ተብሎ ይጠራል። ትክክለኛውን እርዳታ በወቅቱ ማለትም በወጣትነት እድሜ ክልል ማግኘቱ እጅግ በጣም ጠቀሜታ ያለው ሲሆን እርዳታውን በሚመለከት ግን አዋቂዎችንም ጨምሮ ለሁሉም ይሰጣል።

ከዚህ ሌላ ኦቲዝምን በሚመለከት ጠቃሚ መረጃ ለማግኘት በብረንትና (London Borough of Camden) በአካባቢው ለልጆችና ለወጣቶች የተቋቋመው ቡድን የሙዚቃና የስዕል አዝናኝ ፕሮግራም ያለው ሲሆን በየሳምንቱ ለተወሰኑ ሰዓታት የቤት ውስጥ ድጋፍ ይሰጣል። በበለጠ ለመረዳት 0208 458 3259 ይደዉሉ ወይም ድረ ገፅ www.resourcesforautism.org.ukን ይጎብኙ።